# በትራንስፖርት ሚኒስቴር

## የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂ

## የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ

## ቁጥር 1 /2006

መጋቢት 2006 ዓ.ም

# ማ ው ጫ


መግቢያ……………………………………………………………………………………………. 4

<u>ክፍል አንድ፡-</u> 4

ጠቅላላ………………………………………………………………………………………

1 አጭር ርእስ………………………………………………………………………….. 5

2 ትርጓሜ…………………………………………………………………………………… 5

3 የመመሪያው ዓላማ………………………………………………………………………

4 የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን…………………………………………………………… 5

<u>ክፍል ሁለት</u>፡- አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ክፍያ አፈፃፀም

5 የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት …………………………………………………………….. 6

6 የተሸከርካሪ አደጋን ለመድን ሰጪ ሰለማሳወቅ………………………………………………… 6

7 መድን የሌላቸውና ያልታወቁ ተሽከርካሪዎች አደጋን ለኤጀንሲው ስለማሳወቅ…………….. 6

8 ከግዴታ ነፃ የሆነ ተሽከርካሪ ባለቤት……………………………………………………….. 7

9 የአደጋ መረጃ አሰባሰብ……………………………………………………………………… 7

10 የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት፡- የአዋጁ ድንጋጌዎች………………………………………… 8

11 የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ዓይነት…………………………………………………………. 8

12 በአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የማይካተቱ ጉዳዬች………………………………………………. 9

13 የአገልግሎት ክፍያ ስለመጠየቅ……………………………………………………………….. 1

14 ክፍያ ለመጠየቅ የተቀመጠ ቅድመ ሁኔታ…………………………………………………… 1

15 የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄ አቀራረብና የአፈፃፀም ሥርዓት………………………………… 1

16 የክልል ወይም የወረዳ አስተዳደር የጤና ቢሮ…………………………………………………… 1

17 የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር……………………………………………………………………….. 1

18 የሩብ ዓመት ሪፖርት ስለመላክ……………………………………………………………… 1

<u>ክፍል ሦስት</u>፡- የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋምና ማስተዳደር

19 ማቋቋም……………………………………………………………………………………… 1

20 የተዘዋዋሪ ፈንድ አላማ……………………………………………………………………….. 1

21 የተዘዋዋሪ ፈንድ ምንጭና የመጠን ስሌት………………………………………………….. 1

22 የመዋጮ መጠንና ድርሻ የሚወስንበት ጊዜ………………………………………………… 1

23 የመዋጮ መጠንና ድግሻ ስለማሳወቅ……………………………………………………… 1

24 የተዘዋዋሪ ፈንድ የመዋጮ ድርሻ……………………………………………………………. 1

25 የተዘዋዋሪ ፈንዱ ስርጭት……………………………………………………………………. 1

26 የተዘዋዋሪ ፈንዱ ተመንና ድርሻ በአመቱ ከሚቀርበው የአገልግሎት ክፍያ ሲያንስና ሲበልጥ 1

27 በተዘዋዋሪ ፈንዱ የሂሳብ ዘመንና ኦዲት ስለማድረግ……………………………………….. 2

<u>ክፍል አራት፡-</u> የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አፈፃፀም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ

28 የጋራ ኮሚቴው አወቃቀር…………………………………………………………………….. 2

29 የኮሚቴው የግንኙነት ጊዜ…………………………………………………………………….. 2

30 የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት……………………………………………………………….. 2

<u>ክፍል አምስት</u>፡- የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

31 የመድን ፈንድ አስተደደር ኤጀንሲ……………………………………………………….. 2

32 የመድን ሰጪ ኩባንያዎች……………………………………………………………………. 2

33 የጤና ጥበቃ ማኒስቴር……………………………………………………………………….. 2

34 የጤና ቢሮ………………………………………………………………………………… 2

35 የወረዳ ጤና 2

ጽ/ቤት…………………………………………………………………………………………………

36 የሕክምና ተቋማት…………………………………………………………………………………………… 2

37 የፖሊስ ወይም የትራፊክ ፖሊስ…………………………………………………………………………… 2

38 ሌሎች አካላት………………………………………………………………………………………………… 2



<u>ክፍል ስድስት</u>፡- ልዩ ልዩ

39 ቅሬታ አቀራረብ……………………………………………………………………………………………………… 25

40 የተጭበረበሩ ሰነዶችና የሃሰት የክፍያ ጥያቄች……………………………………………………………….. 26

41 የተሻሩ ሕጎች………………………………………………………………………………………………………… 26

42 መመሪያውን ስለማሻሻል……………………………………………………………………………………….. 26

43 መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ………………………………………………………………………………………… 26

44 አባሪዎች

ሀ. የትራፊክ ፖሊስ የአሰቸኳይ ህክፍክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ ……………………………......... 26

ለ. የትራፊክ ፖሊስ የአደጋ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ……………………………………………………………… 26

ሐ. የሕክምና ተቋማት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ መጠየቂያ ቅጽ…………………………….. 26

መ. የሩብ ዓመት የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት የአደጋ ማሳወቂ ቅጽ……………………………………… 26

## መግቢያ

የትራንስፖርት ሚኒስቴር የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ስልጣን እና በአንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት በተሽከርካሪ አደጋ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ለማድረግና የህክምና ተቋማት ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በወቅቱ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ አሠራር ለመዘርጋትና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ኃላፊነትን ግልጽ በሆነ መንገድ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በትራንስፖርት ሚኒስቴር የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት አፈፃፀም መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በፌደራል መንግስት "የተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

1) **"ቢሮ"** ማለት የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ነው፡፡

2) **"የህክምና ተቋም"** ማለት ማንኛውም ከኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒት፣ የጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለስልጣን ወይም ከክልልና ከከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ህጋዊ ፈቃድ በማግኘት የህክምና አገልግሎት የሚሰጥ የግል፣ ወይም የመንግስት የህክምና ተቋም ነው፡፡

3) **"አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 799 /2005 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 16 መሠረት በመንገድ ላይ በደረሰ በተሽከርካሪ አደጋ የተጎዳ ግለሰብ ከአደጋው ቦታ ወደ ህክምና ተቋም በሚጓጓዝበት ወቅት እና በህክምና ተቋሙ ድንገተኛ ክፍል ውስጥ የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት ነው፡፡

4) **"ተዘዋዋሪ ፈንድ"** ወይም **"ተዘዋዋሪ ገንዘብ"** ማለት የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አፈፃፀምን በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ በዚህ መመሪያ መሰረት ከመድን ሰጪ ኩባንያዎች፣ ከአዋጁ ድንጋጌዎች ነጻ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ባለንብረቶች ወይም አስተዳዳሪዎችና ከኤጀንሲው በሚገኝ መዋጮ የሚቋቋምና በየጊዜው የሚተካ ወይም የሚወራረድ የገንዘብ ምንጭ ነው፡፡

5) **"ተጎጂ"** ማለት በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው ነው፡፡

6) **"የፆታአገላለፅ "** በወንድ ፆታ የተገለጹት በሙሉ ለሴት ፆታ ያገለግላሉ፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በተሽከርካሪ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት በህክምና ተቋማት ማግኘቱን ለማረጋገጥ፣ አገልግሎት የሰጠው የህክምና ተቋም ተገቢና ወቅታዊ ክፍያ እንዲያገኝ ለማድረግና፣ የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት በማሳወቅ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚነት ያለው ግልጽ የሆነ አንድ ወጥ አሠራር ለማስቀመጥ ነው፡፡

4. **የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት ማንኛውም ሰው የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ለመስጠት በማንኛውም የህክምና ተቋም፣ በፖሊስ፣ በትራፊክ ፖሊስ፣ በመድን ሰጪ ኩባንያ፣ በኤጀንሲው፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በጤና ቢሮዎች፣ እንዲሁም በተሽከርካሪ ባለንብረት፣ በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ተጎጂ ወይም በዚህ መመሪያ መሠረት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት እና ክፍያ የመጠየቅ መብት ባለው ማንኛውም አካል ወይም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ክፍያ አፈፃፀም

### ንዑስ ክፍል አንድ

### የተሽከርካሪ አደጋን ስለማሳወቅ

5. **የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት**

የተሽከርካሪ አደጋ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ሥራ የሚጀመረው በተሽከርካሪ አደጋ መከሰት ምክንያት ሲሆን በንብረት ብቻ ላይ ከደረሰ ጉዳት በስተቀር ሌሎች በሰው ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች አገልግሎቱ ለማንኛውም ተጎጂ በህክምና ተቋማት እንዲሰጥ ምክንያት ይሆናል፡፡

6. **የተሽከርካሪ አደጋን ለመድን ሰጪ ስለማሳወቅ**

   1. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 5 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር መድን ገቢው መድን የተገባለት ተሽከርካሪ አደጋ ማድረሱን ወዲያውኑ ወይም ቢዘገይ በ10 ቀን ውስጥ ለመድን ሰጪው ማሳወቅ አለበት፡፡

   2. የአደጋ ማሳወቂያው መንገድ በእያንዳንዱ የመድን ሰጪ ኩባንያ ጥቅም ላይ እንዲውል በተፈቀደ ማንኛውም ዘዴ ወይም የአደጋ ማሳወቂያ ቅጽ በመሙላት ለሚመለከተው የመድን ሰጪ ኩባንያ በተመዘገበ አድራሻ በማቅረብ ሊሆን ይችላል፡፡

3. ኤጀንሲው ከመድን ሰጪዎች ጋር በጋራ በመስራት የኩባንያዎችን ስምና የተመዘገበ አድራሻ እንዲሁም ሌላ ለግንኙነት የሚያስፈልግ መረጃ በማዘጋጀት በየወቅቱ ሕብረተሰቡ እንዲያውቀው ያሰራጫል፡፡

## 7. መድን የሌላቸውና ያልታወቁ ተሽከርካሪዎች አደጋን ለኤጀንሲው ስለማሳወቅ

1. መድን በሌላቸው ወይም ባልታወቀ ተሽከርካሪ የደረሰ አደጋን አሽከርካሪው ወይም ባለንብረቱ ወይም ተጎጂው፣ ወይም አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የሰጠው ወገን፣ ወይም ፖሊስ ወይም ትራፊክ ፖሊስ ወይም ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. የመድን ፈንድ ክፍያዎች አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 8 ላይ አደጋን ስለማሳወቅ በተገለፀው መሠረት ለኤጀንሲው ዋና መ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ላለው የኤጀንሲው ቅርንጫፍ ወይም በኤጀንሲው ለተወከለ መድን ሰጪ ወይም የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ለሰጠው ተቋም ወይም ለተጎጂው ሕጋዊ ተወካይ በማሳወቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡
3. አደጋውን የሚያሳውቀው በኤጀንሲው የተመዘገበ ትክክለኛ አድራሻ ሲሆን በስልክ፣ በፋክስ ወይም ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው መድን የሌለው ወይም ያልታወቀ ተሽከርካሪ የአደጋ ማሳወቂያ ወይም የትራፊክ ፖሊስ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ መሠረት ሊሆን ይችላል፡፡

## 8. ከግዴታ ነፃ የሆነ የተሽከርካሪ ባለቤት

1. በአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በሚኒስቴር መ/ቤቱ መድን ከመግዛት ድንጋጌ ነፃ በሆነ ተሽከርካሪ ስለደረሰው አደጋ ባለንብረቱ ወይም ተቋሙ ወይም አሽከርካሪው ወይም ፖሊስ ወይም ትራፊክ ፖሊስ ወይም ሌላ የሚመለከተው ሰው ማሳወቅ አለበት፡፡
2. አደጋውን የማሳወቂያ መንገድ ለኤጄንሲው ወይም በኤጄንሲው የተወከለው አካል በሚያወጣው ቅጽ ወይም በስልክ ወይም በፋክስ ይሆናል፡፡

## 9. የአደጋ መረጃ አሰባሰብ

1. በአዋጁ አንቀጽ 11 መሰረት መረጃ መስጠትን በተመለከተ መድን ገቢው የጉዳት ካሳ እንዲከፈለው ተጎጂው ወይም መብት ባለው ወገን ሲጠየቅ ተሽከርካሪው መድን ያለው ወይም የሌለው መሆኑንና የመድን ምስክር ወረቀቱ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 9 ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች በመግለጽ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

2. በአዋጁ አንቀጽ 13 የመድን ተለጣፊ አለመያዝ እና አለመኖር የመድን ሽፋን እንደሌለው ስለሚያስቆጥረው የመድን የምስክር ወረቀት እስኪመጣ ድረስ ፖሊስ ተሽከርካሪውን ይዞ ለማቆየት ስልጣን ያለው ሲሆን ይህንን ሁኔታ ኤጄንሲው እንዲያውቅ መደረግ አለበት፡፡

3. በኤጀንሲው የተዘጋጀውና በትራፊክ ፖሊስ የህክምና ተቋሙ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት እንዲሰጥ የሚተላለፈው የመጠየቂያ ቅጽ እንደ አደጋ ማሳወቂያ ቅጽ እና የአደጋ መረጃ ምንጭ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል፡፡

4. የትራፊክ ፖሊስ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ መኖር መድን ላላቸው ወይም መድን ለሌላቸውና ገጭተው ላመለጡ እንዲሁም ከአዋጁ ድንጋጌ ነፃ ለተደረጉ ተሽከርካሪዎች በሙሉ አደጋ ለማሳወቅና ክፍያ ለመጠየቅ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በመስጠት ያገለግላል፡፡

## 10. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት

1. በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው እስከ ብር 2,000.00 ድረስ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የማግኘት መብት አለው፡፡

2. በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ማንኛውም የህክምና ተቋም የተሽከርካሪ አደጋ ደርሶበት ወደ ህክምና ተቋም ለመጣ ማንኛውም ተጎጂ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

3. በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የሰጠ የህክምና ተቋም ለአገለልግሎቱ ያወጣውን ወጪ በዚህ መመሪያ ላይ በተገለጸው መሰረት እንዲከፈለው መጠየቅ ይችላል፡፡

## 11. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ዓይነት

1. የአስቸኳይ ህክምና በአደጋው ቦታ የሚደረግ የመጀመሪያ ደረጃ ህክምና፣ ከአደጋው ቦታ ወደ ህክምና ተቋማት ተጎጂው በሚወሰድበት ወቅት የተሰጠ የአምቡላንስ አገልግሎትና በጉዞው ወቅት የሚደረግ የባለሙያ የህክምና አገልግሎት እና በህክምና ተቋም የድንገተኛ ክፍል (Emergency Ward (ED)) ውስጥ በባለሙያ የሚሰጥ የነፍስ አድን የህክምና አገልግሎት ነው፣
2. በህክምና ተቋም የድንገተኛ ክፍል (Emergency Ward (ED)) ውስጥ በባለሙያ የሚሰጥ የነፍስ አድን የህክምና አገልግሎት በሚከተሉት ሶስት ቦታዎች ሊሰጥ ይችላል፡ -

   ሀ. የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ በባለሙያ ነርስ የሚደረግበት ቦታ"The triage area"፣

   ለ. የተለያዩ የነፍስ አድን ሥራዎች የሚካሄዱበት ቦታ፣ "The resuscitation area"

   ሐ. በድንገተኛ ክፍል በሚገኝ ተሽከርካሪ ጎማ ያለው አልጋ (Gurney) ወይንም ተጎታች ጋሪ (Trolley) ተጎጂው የሚያርፍበት ቦታ "The major or general medical area"

3. ከላይ የተገለጹት የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ዓይነቶች በሙሉ በአንድ የህክምና ተቋም ወይንም በተለያዩ የህክምና ተቋማት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ የህክምና ተቋም እንደሰጠው አገልግሎት ክፍያ የመጠየቅ መብት አለው፡፡

5. በድንገተኛ ክፍል ለተጎጂው ህክምና እየሰጠው ያለው የሕክምና ባለሙያ ልዩ ህክምና እንዲያገኝ ወይም በህክምና ተቋሙ ተኝቶ ወይም በተመላላሽነት እንዲታከም ውሳኔ ሲሰጥ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎቱ ያበቃል፡፡

6. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ወጪ ከአካል ጉዳት እና ከሞት ጉዳት ካሣ ላይ ተቀናሽ አይደረግም፤ ወይም በጉዳት ካሣ ስሌቱ ውስጥ አይካተትም፡፡

12.በአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ውስጥ የማይካተቱ ጉዳዮች

1. የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አጠቃላይ ወጪ ከብር 2,000.00 በላይ ከሆነ ልዩነቱን የተሽከርካሪው ባለንብረት ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ልዩነቱን ይከፍላል፡፡

2. ተጎጂው የላቀና ልዩ የህክምና አገልግሎት ወይም በህክምና ተቋም ውስጥ ተኝቶ ወይም በተመላላሽነት በመታከሙ ምክንያት የመጣ የህክምና ወጪ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ስላልሆነ ከሌሎች የጉዳት ዓይነቶች ማለትም የአካል ጉዳት ወይም የሞት ካሣ ላይ ተቀንሶ የሚከፈለው ነው፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ የተገለፀው የህክምና ወጪ በሚከተሉት ወገኖች የሚሸፈን ይሆናል፡-

ሀ. መድን ባላቸው ተሽከርካሪዎች በደረሰ አደጋ የመጣ ጉዳት ከሆነ የመድን ሽፋኑንና የምስክር ወረቀቱን በሰጠው የመድን ሰጪ ኩባንያ፣

ለ. መድን በሌለውና ባልታወቀ ተሽከርካሪ አደጋ የደረሰ ጉዳት ከሆነ በኤጀንሲው

ሐ. በአዋጁ መሠረት የ3ኛ ወገን የተሽከርካሪ አደጋ የመድን ሽፋን እንዲገቡ በማይገደዱ ተሽከርካሪዎች የደረሰ ጉዳት ከሆነ በተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም በወኪሉ።

4. ሌላ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ከአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ውጭ ለሚደረግ የሕክምና ወጪ ከሌሎች የጉዳት ካሳ ክፍያዎች ጋር ተደምሮ በአዋጁ አንቀጽ 16(1) ላይ ከተገለጹት የኃላፊነት መጠን በላይ የመድን ውል የሰጠው ኩባንያ ወይንም ኤጀንሲው የመክፈል ግዴታ የለባቸውም፡፡

5. በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (1) እና (2) ላይ ከተቀመጠው ኃላፊነት በላይ የሚመጣ ማንኛውም ዓይነት የጉዳት ካሳ በተሽከርካሪው ባለቤት ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ኃላፊነት በተጣለበት ወገን የሚሸፈን ወይም የሚከፈል ይሆናል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀምና ተፈላጊ መረጃዎች

### 13. የአገልግሎት ክፍያ ስለመጠየቅ

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ማንኛውም የህክምና ተቋም የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ ሊጠይቅ የሚችለው በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት በማንኛውም ሰው ላይ ለደረሰ ጉዳት ለተሰጠ አገልግሎት ብቻ ነው፡፡
2. በሕክምና ተቋም የሚሰጠው የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መፈፀም አለበት፡፡
3. ማንኛውም አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የሰጠ የህክምና ተቋም ክፍያ ሊጠይቅ የሚችለው የሚከተሉትን አካላትን ነው፡ -

   ሀ. በዘጠኙ ክልሎች የሚገኙ የጤና ተቋማት በሚገኙበት ቦታ ያለውን “የወረዳ ጤና ጽ/ቤት” ን

   ለ. በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የጤና ተቋማት በሚገኙበት ከተማ “የአስተዳደሩን የጤና ቢሮ” ሲሆን እንደአግባብነቱ የጤና ቢሮዎቹ ከኤጀንሲው ጋር በሚያደርጉት ስምምነት ከዚህ የተሻለ አሰራር ተግባራዊ ሊደርጉ ይችላሉ፡፡

   ሐ. በፌዴራል መንግስት በሚገኝ ሆስፒታል ለተሰጠ አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርን ሊጠይቁ ይችላል፡፡

### 14. ክፍያ ለመጠየቅ የተቀመጠ ቅድመ ሁኔታ

አስቸኳይ የህክምና አገልግሎት የሰጠ ማንኛውም ተቋም ለሰጠው አገልግሎት ክፍያ ለመጠየቅ፣

1. በዚህ መመሪያ ላይ የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ሙሉ በሙሉ መከተል፣

2. በዚህ መመሪያ መሠረት የተዘጋጀውን የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ መጠየቂያ ቅፅ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ቅጾችን እንዲያያዝ ማድረግ፣

3. ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መረጃዎችን ማጠናከርና ተጎጂው ህክምና በሚያገኝበት ድንገተኛ ክፍል ውስጥ በግልጽ ሊታይ በሚችል ቦታ በሚለጠፍ ፖስተር ላይ ይጻፋል፡፡

ሀ. የተጎጂውን ስምና ሙሉ አድራሻ፣

ለ. ተጎጂው በተሽከርካሪ አደጋ የተጎዳ መሆኑን በሚገኙ መረጃዎች ማጣራትና የአደጋውን ቀን፣ የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር፣ አደጋው የደረሰበትን ቦታ እና ሰዓት ፣

ሐ. ለአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ተጎጂውን ወደ ህክምና ተቋሙ የላከውን ትራፊክ ፖሊስ፣ ፖሊስ ወይም ግለሰብ ስምና ሙሉ አድራሻ፣ የትራፊክ ፖሊስ ከሆነ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ እንዲቀርብ ማድረግና ማያያዝ፣

መ. አደጋው የደረሰው መድን በገባ ተሽከርካሪ ከሆነ የመድን ሰጪው ኩባንያው ስምና የመድን የምስክር ወረቀት ቁጥር፣

ሠ. አደጋው የደረሰው መድን በሌለው ተሽከርካሪ ከሆነ የተሽከርካሪውን ባለቤት ወይም የአሽከርካሪውን ስምና አድራሻ እንዲሁም የተሽከርካሪውን የሰሌዳ ቁጥር፣

ረ. አደጋው የደረሰው ባልታወቀ ተሽከርካሪ ከሆነ ጉዳዩን የመዘገበው የትራፊክ ፖሊስ ወይንም ወደ ህክምና ተቋሙ ያመጣውን ሰው ስምና አድራሻ፣

4. አስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ በመጠየቂያ ቅጽ ተሞልቶ እና በሕክምና ተቋሙ ኃላፊ ተፈርሞ ለተጎጂው የተሰጠውን አገልግሎትና የወጪ ዝርዝር ከተፈላጊ ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች ጋር በአግባቡ በመሙላት በአባሪነት ማያያዝና ማቅረብ ያለበት ሲሆን ከማስረጃዎቹ መካከልም እንደአግባብነቱ፣

ሀ. የሀኪም ትዕዛዝ፣ የሀኪም የምስክር ወረቀት፣ ደረሰኝ የመድሀኒት ወይም የላብራቶሪ ምርመራ ክፍያና ሌሎች ሰነዶችን፣

ለ. የትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት፣ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ፣ የአስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት ክፍያ መጠየቂያ ቅጽ እና የትራፊክ ፖሊስ የአደጋ ሪፖርት ናቸው፡፡

## 15. የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄ አቀራረብና የአፈፃፀም ሥርዓት

1. ማንኛውም የሕክምና ተቋም አገልግሎት የሰጠበት ወር ባለቀ 10 ቀን ውስጥ በዚህ መመሪያ በተዘረዘረው መሠረት በአንቀጽ 13 ለተመለከተው አካል የክፍያ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

2. የክፍያ ጥያቄውና አባሪ ሰነዶች የሚቀርቡት ለዚሁ ተግባር ተብሎ በተሰራጨው የአስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት ክፍያ መጠየቂያ ቅጽ ላይ አስፈላጊ መረጃዎች ተሞልተውና በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ የሕክምና ተቋሙ ማህተምና የኃላፊው ፊርማ መኖር አለበት፡፡

3. ከተገለፀው የ10 ቀን የጊዜ ገደብ ከአልፈ በኋላ በተንጠባጠበ መንገድ የሚቀርቡ የክፍያ ጥያቄዎችና አባሪ ሰነዶች ሊስተናገዱ የሚችሉት በሚቀጥለው ወር ይሆናል፡፡

4. የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄ በአካባቢው ከሚገኙ የህክምና ተቋሞች የቀረበለት በክልል የሚገኝ የወረዳ ጤና ቢሮ አስፈላጊውን ማጣሪያ ካደረገ በኋላ በሸኚ

ደብዳቤ ሰነዶቹ በደረሱት በ10 የሥራ ቀን ውስጥ ክፍያው አገልግሎት በሰጠው ተቋም ስም እንዲፈፀም ለክልሉ የጤና ቢሮ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

5. የወረዳው የጤና ጽ/ቤት የሚከተሉትን የማጣራት ተግባር ያከናውናል፡፡

   ሀ. የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄውና በአባሪነት የተያያዙት ሰነዶች ትክክለኛነት፣

   ለ. የክፍያው ጥያቄ አቀራረብ በዚህ መመሪያ ላይ በተዘረዘረው መሠረት እንደሆነ እና

   ሐ. የቀረበው የክፍያ ጥያቄ በዓመቱ ውስጥ ከተስተናገዱ የክፍያ ጥያቄዎች ጋር ተደምሮ በወረዳው ለሚገኙ የጤና ተቋማት በዓመቱ መጀመሪያ ላይ በጥቅል ከተመደበው የተዘዋዋሪ ፈንድ የማይበልጥ መሆኑን

6. አጠራጣሪ እና ያልተሟላ መረጃ ያለው የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የክፍያ ጥያቄ ደግሞ ሁኔታውን ዘርዝሮ በመግለጽ ሰነዱን ለሚመለከተው የህክምና ተቋም ወዲያውኑ በሸኚ ደብዳቤ ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

7. በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬዳዋ ከተማ ያሉ የአስተዳደር ጤና ቢሮዎች በተመሳሳይ ሁኔታ በአስተዳደሩ ክልል በሚገኙ የሕክምና ተቋማት የቀረበላቸውን የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄና አባሪ ሰነዶች በማጣራት ተገቢውን ክፍያ በ20 የሥራ ቀን ውስጥ መፈፀም ያለባቸው ሲሆን፣

   ሀ. የሚጣሩት ጉዳዮች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15/5/ ስር የተገለፁት ተግባራት መሟላታቸውን ማረጋገጥ፣

   ለ. አጠራጣሪና ያልተሟላ መረጃ ያላቸው የክፍያ ጥያቄዎች ለሚመለከተው የጤና ተቋም በሸኚ ደብዳቤ አማካኝነት በዚሁ የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተካክለው እንዲያቀርቡ መላክ አለባቸው፡፡

## 16. የክልል ወይም የከተማ አስተደደር የጤና ቢሮ

የክልል ወይም የከተማ አስተደደር የጤና ቢሮ ከተለያዩ የህክምና ተቋማት የቀረበለትን የአገልግሎት ክፍያ በፈፀመ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ተገቢ የሆኑ ሰነዶችን በሙሉ በማያያዝ በሸኚ ደብዳቤ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡

17. **የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር**

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የአገልግሎት ክፍያ የተፈፀመባቸው ሰነዶች በደረሱት 10 የሥራ ቀን ውስጥ በማጣራትና በመለየት ለሚመለከታቸው አካላት ማለትም ለሚመለከተው የመድን ሰጪ ኩባንያ ወይንም ለመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ይልካል፡፡

18. **የሩብ ዓመት ሪፖርት ስለመላክ**

1. **የክልልና የወረዳ ጤና ጽህፈት ቤቶች**

ሀ. በክልል የሚገኝ የወረዳ ጤና ተቋም የሩብ ዓመቱ ባለቀ በ10 ቀናት ውስጥ የተፈፀመ የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርት አጠናቅሮና አዘጋጅቶ ለክልሉ የጤና ቢሮ መላክ አለበት፡፡

ለ. የክልሉ የጤና ቢሮ በየሩብ ዓመቱ የተከፈሉ የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርት ከየወረዳዎቹ በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ በማደራጀት ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡

2. **በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች**

የአስተዳደሩ የጤና ቢሮ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሚገኝ የወረዳ ጤና ተቋማት የተፈፀመውን የአገልግሎት ክፍያ መረጃ የያዘ ሪፖርት በማጠናቀርና በማዘጋጀት የሩብ ዓመቱ ባለቀ በ20 ቀናት ውስጥ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡

3. **የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር**

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሩብ ዓመቱ ባለቀ በ30 ቀናት ውስጥ ከክልልና ከሁለቱ የከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮዎች የተላኩለትን የሩብ ዓመት የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርት ለኤጀንሲው ይልካል፡፡

4. **ኤጀንሲው**

ሀ. ኤጀንሲው የሩብ ዓመት የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርት ተጠቃሎ በደረሰው በ10 ቀናት ውስጥ በክልልና በከተማ አስተደደር የተደረገውን የክፍያ አፈፃፀም ከተያዘው የተዘዋዋሪ ፈንድ ጋር የሚያነፃፅር አጠቃላይ ሪፖርት በማዘጋጀት ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡

ለ. በተለይም በሁለተኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ አጠቃላይ የአገልግሎት ክፍያ መግለጫ ሪፖርት በሚያጠናቅርበት ወቅት በአንደኛውና በሁለተኛው የሩብ ዓመት የክፍያው መጠን በስሌት ከተገመተው የተዘዋዋሪ ፈንድ ጋር ሲነፃፀር 3/4ኛ ወይም 75% ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑን መረጃዎች ከጠቆሙ ለቀረው ዘመን የሚሆን ማስተካከያ የተዘዋዋሪ ፈንድ መጠንና እያንዳንዱ የሚመለከተው ወገን የመዋጮ ድርሻውን ያሳውቃል፡፡

ሐ. በሶስተኛው ሩብ ዓመት ተከታታይ የሩብ ዓመት የአገልግሎት ክፍያዎች ከተያዘው የፈንድ ተመን ሲነፃፀር 3/4 ወይም 75% ሆኖ ከተገኘ በተመሳሳይ መንገድ ለቀሪው ጊዜ የሚያስፈልገውን የፈንድ መጠንና ለሚመለከታቸው ወገኖች የመዋጮ ድርሻቸውን ያሳውቃል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ተዘዋዋሪ ፈንድ ማቋቋምና ማስተዳደር

19. ***መቋቋም***

የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት ተዘዋዋሪ ፈንድ ከዚህ በኋላ ተዘዋዋሪ ፈንድ እየተባለ የሚጠራ የገንዘብ ምንጭ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡

20. **የተዘዋዋሪ ፈንዱ ዓላማ**

የተዘዋዋሪ ፈንዱ አላማ በተሽከርካሪ አደጋ የሶስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 27 የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡

## 21. የተዘዋዋሪ ፈንዱ ምንጭና የመጠን ስሌት

1. የተዘዋዋሪ ፈንዱ ከመድን ሰጪ ኩባንያዎችና ከመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የሚሰበሰብ ዓመታዊ መዋጮ ነው፡፡

2. የእያንዳንዱ የመድን ሰጪ የመዋጮ ድርሻ የሚወሰነው በሀገር ዓቀፍ ደረጃ በፌዴራል ፖሊስ ባለፈው ዓመት በተሰበሰበ የትራፊክ አደጋ መረጃን፣ በኩባንያዎቹ የተሸከርካሪ መድን የገበያ ድርሻ ማለትም በመድን የምስክር ወረቀት እና የመድን ተለጣፊ አጠቃቀም ላይ ተመርኩዞ የሚሰላ ይሆናል፡፡

3. የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ የመዋጮ ድርሻ የሚወሰነው በተመሳሳይ ሁኔታ በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ከፌደራል ፖሊስ በተሰበሰበ ያለፈው ዓመት የትራፊክ አደጋ ሲሆን በስሌቱ ወቅት፡-

   ሀ. ባልታወቁ ተሽከርካሪዎች የደረሱ አደጋዎችና የተጎጂዎች ቁጥር እንዲሁም፣

   ለ. መድን በሌላቸው ተሽከርካሪዎች ሊደርሱ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ አደጋዎችና የተጎጂዎች ቁጥር ለዚሁ ተብሎ በሚሰበሰብ መረጃ ላይ ተመርኩዞ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 22. የመዋጮ መጠንና ድርሻ የሚወሰንበት ጊዜ

የተዘዋዋሪ ፈንዱ መጠንና ገቢ የሚሆነው የመዋጮ ድርሻ በየዓመቱ ባለ የመጀመሪያ ወር ላይ ሆኖ ኤጀንሲው በሚያደርገው ጥናት ላይ ተመርኩዞ ቦርዱ በሚወስነው መሠረት ነው፡፡

## 23.የመዋጮ መጠንና ድርሻ ስለማሳወቅ

ኤጀንሲው በዚህ መንገድ የተሰላውን የተዘዋዋሪ ፈንድ መጠንና የመዋጮ ድርሻ ቦርዱ ውሳኔ በሰጠ በ24 ሰአት ውስጥ ለሚመለከተው አካል በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

## 24. የተዘዋዋሪ ፈንድ የመዋጮ ድርሻ

1. በተዘዋዋሪ ፈንድ የመዋጮ ድርሻ ገቢ የሚደረጉ ክፍያዎች ተቀማጭ የሚሆነው ለዚሁ ተብሎ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ውስጥ ነው፡፡

2. በአንቀፅ 24 የተሰላው ዓመታዊ የመዋጮ ድርሻ ለተዘዋዋሪ ፈንዱ በተከፈተው የሂሳብ አካውንት ውስጥ በተጠቀሱት አካላት ከዚህ በታች በተገለፁት የሩብ ዓመት የመጀመሪያ ወራት ላይ ቀጥሎ እንዲተመለከተው ገቢ መድረግ አለባቸው፡-

| | |
|---|---|
| ሀ. አንደኛ /የመጀመሪያ ሩብ ዓመት | ከመስከረም 25 -30 |
| ለ. ሁለተኛ ሩብ ዓመት | ከታህሳስ 25-30 |
| ሐ. ሶስተኛ ሩብ ዓመት | ከመጋቢት 25 — 30 |
| መ. አራተኛ ሩብ ዓመት | ከሰኔ 25 -30 |

3. በተጠቀሱት የክፍያ ወቅቶች ውስጥ የሚደርስበትን መዋጮ ገቢ ያላደረገ የመድን ውል ሰጭ ኩባንያ ክፍያውን ለሚያዘገይበት ጊዜ በተጨማሪ ሊከፍል ስለሚገባው ክፍያ ከኤጀንሲው ጋር በሚደረግ ውል ይወሰናል፡፡

4. የመዋጮ ክፍያውን ለሁለት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ የሚያዘገይ የመድን ሰጭ ኩባንያ የተቀመጠውን የክፍያ ጊዜ ጠብቆ ገቢ እንዲያደርግ ኤጀንሲው በፅሁፍ ያሳውቀዋል፡፡ የማያሻሽል ከሆነም በአዋጁ አንቀፅ 30 መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 25. የተዘዋዋሪ ፈንዱ ሥርጭት

1. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ የሆነው የተዘዋዋሪ ፈንዱ መዋጮ ባለፉት ዓመታት ከፌዴራል ፖሊስ በተሰበሰበ የትራፊክ አደጋ መረጃ ላይ ተመርኩዞ በሚደረግ ስሌት መሠረት ለዘጠኝ ክልል እና ለሁለት የከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮዎች ይከፋፈላል፡፡

2. በዚህ መንገድ ለክልል እና ለከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮዎች ተሰልቶ የሚመደበው የተዘዋዋሪ ፈንድ ድርሻ ተቀማጭ የሚሆነው በሚመለከተው የጤና ቢሮ ስም ለዚሁ ተብሎ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ነው፡፡

3. በክልል እና በከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮዎች ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ የሚሆነው የተዘዋዋሪ ፈንድ ድርሻ በክልሉ ወይንም በከተማ አስተዳደሩ ሥር ባሉ ወረዳዎች ደርሰዋል ተብለው በተመዘገቡና በክልሉ ወይንም በፌደራል ፖሊስ ከተሰበሰቡ የትራፊክ አደጋዎች እና በተጎጂዎች ቁጥር ላይ ተመርኩዞ በማስላት ለየወረዳዎቹ የሚመደብ ሲሆን፣

   ሀ. በክልል ለሚገኙ የወረዳ የጤና ፅ/ቤቶችና የተሰላው የተዘዋዋሪ ፈንድ ድርሻ ገቢ ወይም ተቀማጭ የሚሆነው በሚመለከተው ክልል ጤና ቢሮ ስም ለዚህ ጉዳይ ተብሎ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ነው፡፡

   ለ. በእያንዳንዱ ወረዳ ሥር ባሉ የሕክምና ተቋማት የአገልግሎት ክፍያ ሲፈፀም በክልሉ ጤና ቢሮ የባንክ ሂሳብ ለወረዳው ለወቅቱ በታሳቢነት ከተያዘለት ወይም ከተመደበለት ገንዘብ ይቀነሳል፡፡

   ሐ. እያንዳንዱ ወረዳ በዚያ ዓመት በተጠባባቂነት ከተያዘለት ወይም ከተመደበለት የፈንድ ድርሻ በላይ ለመጠቀም የክፍያ ጥያቄ ከቀረበ ጉዳዩን የክልሉ የጤና ቢሮ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

   መ. የጤና ጥበቃ ሚ/ር የጋራ ኮሚቴውና በኤጀንሲው ውሳኔ መሠረት የአገልግሎት ክፍያው ጥያቄ ይስተናገዳል፡፡

4. ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለክልል ወይንም ለከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮዎች የሚሰራጨው እንዲሁም በተዋረድ ከክልልና ከከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮዎች ለወረዳ ጤና ተቋማት በታሳቢነት የሚያዘው የተዘዋዋሪ ፈንድ ድርሻ የሚወሰነው ኤጀንሲው የተዘዋዋሪ ፈንዱን መጠን ለማስላት በየዓመቱ ከሚያደርገው ጥናት ጋር በአንድነት ሲሆን የሚወሰነውም በቦርድ ነው፡፡

## 26. የተዘዋዋሪ ፈንድ ክፍያ ማነስ ወይም መብለጥ

1. **የተዘዋዋሪ ፈንድ ተመን ክፍያ ማነስ**

ሀ. በአጠቃላይ ለዓመቱ ሊበቃ ይችላል ተብሎ የተሰላው የተዘዋዋሪ ፈንድ መጠን በጥቅሉ አንሶ ሲገኝ ተጨማሪ የመዋጮ ክፍያ በሚመለከታቸው አካሎች ተፈፃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ለ. የተጨማሪ አጠቃላይ የተዘዋዋሪ ፈንድ ተመኑ መጠን ከዚህ እንደሚከተለው ይሰላል፡፡

| ለዓመቱ የተተመነው አጠቃላይ የተዘዋዋሪ ፈን የገንዘብ መጠን / 365 ቀናት | X | በዓመቱ ያሉ ቀሪ ቀናትቀናት |
|---|---|---|

ሐ. በዚህ መንገድ የተሰላው አጠቃላይ የተዘዋዋሪ ፈንድ ተመን መጠን በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ለስሌት በተወሰዱ መለኪያዎች ማለትም የመድን ምስክር ወረቀትና የመድን ተለጣፊ አጠቃቀም ብዛት፣ መድን የሌላቸውና ያልታወቁ ተሽከርካሪዎች ግምታዊ ብዛት ላይ ተመስርቶ ለሚመለከተው ለእያንዳንዱ አካል የመዋጮ ድርሻ ይተመናል፡፡

መ. የተተመነው ተጨማሪ የተዘዋዋሪ ፈንድ መጠንና ድርሻ እንዲሁም ስርጭት በቦርድ በተፈቀደ በ24 ሰአት ውስጥ ለሚመለከታቸው አካላት ኤጀንሲው በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

ሠ. የዚህን የመዋጮ ድርሻ ኤጀንሲው በደብዳቤ ባሳወቀ በ10 ቀናት ውስጥ ለዚሁ በተከፈተው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሂሳብ ቁጥር ውስጥ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

2. **የተዘዋዋሪ ፈንድ ተመን ከአገልግሎት ክፍያ መብለጥ**

ሀ. ለዓመት እንዲሆን የተሰላው የተዘዋዋሪ ፈንድ ኦዲት ከተደረገ በኋላ ትርፍ ከተገኘ ለሚቀጥለው ዓመት እንዲንከባለል ይደረጋል፡፡

ለ. የሚንከባለለው በትርፍ የተያዘ ተዘዋዋሪ ፈንድ መጠን ለዓመቱ ከሚሰላው ተመን ላይ ተቀናሽ ስለሚሆን የሚመለከታቸው አካላት በእያንዳንዳቸው ለመጭው ዘመን

ከሚመደብባቸው የመዋጮ ድርሻ ላይ በዚሁ ትርፍ መጠን እንዲቀንስላቸው ይደረጋል፡፡

27.የተዘዋዋሪ ፈንድን ኦዲት ስለማድረግ

1. የተዘዋዋሪ ፈንዱ የሂሳብ ዘመን በየዓመቱ ከመስከረም 1 ቀን በመጀመር እስከ ጳጉሜ 5/6 ድረስ ይሆናል፡፡
2. የተዘዋዋሪ ፈንዱ ዓመቱ ባለቀ የመጀመሪያው ወር ላይ ኦዲት ያደርጋል
3. የኦዲት ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲሁም ለቦርድ ቀርቦ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የባለድርሻ አካላት በተገኙበት የጋራ ውይይት ይደረግበታል፡፡
4. የኦዲት ሪፖርቱ ለመጪው ዘመን የተዘዋዋሪ ፈንድ ትመናና የአገልግሎት ክፍያ እንዲሁም ሌሎች ተግባራት መሠረታዊ ግብዓት በመሆን ያገለግላል፡፡

## ክፍል አራት

### የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎት አፈፃፀም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ

28.የጋራ ኮሚቴ አወቃቀር

1. የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም መመሪያውን ተግባራዊነት የሚያረጋግጥ እና የሚቆጣጠር የጋራ ኮሚቴ በሚከተሉት አካላት በሚወከል አራት አባላት ይቋቋማል፡ -

   ሀ. መድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ፡ - ሰብሳቢ

   ለ. ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፡ - ጸሐፊ

   ሐ. የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ፡ - አባል

   መ. የመድን ሰጪ ኩባንያዎች ፡ - አባል

   ሠ. መድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ፡ - አባል

2. የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ይሆናል፡፡

3. በተለያዩ ምክንያቶች ከጋራ ኮሚቴው አባል ሲወጣ በጎደለው አባል ምትክ የሚመለከተው ወገን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መተካት አለበት፡፡

## 29. የኮሚቴው የግንኙነት ጊዜ

1. የጋራ ኮሚቴው በተቋቋመ በአንድ ወር ውስጥ ለአገልግሎቱ ዘመን የሚሆን የስራ እቅድና መርሃ ግብር በማውጣት ለኤጀንሲው ያቀርባል፡፡

2. ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው በመደበኛነት በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ነገር ግን እንደ አስፈላጊነቱ ከዚህ ባነሰ ጊዜ በመሰብሰብ ሥራውን በማከናወን የተጣለበትን ኃላፊነት ይወጣል፡፡

## 30.የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

ኮሚቴው ከዚህ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፣

1. በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች በዚህ መመሪያና በአዋጁ መሰረት የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ማግኘታቸውን ይገመግማል፣

2. በአሰራር ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን በመገምገም ማስተካከያ አርምጃ መውሰድ እና ከኮሚቴው አቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮችን ለኤጀንሲው ያቀርባል፣

3. ለአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የተመደበው ገንዘብ በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ በተዘረዘረው መሰረት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤ ያጋጠሙ ችግሮችንና የተገኙ ውጤቶችን በየሩብ ዓመቱ ለኤጀንሲው ሪፖርት ያቀርባል፣

4. ከኤጀንሲው ጋር በመሆን የተዘዋዋሪ ፈንድ መጠን ትመናና ማስተካከያ ጥናት ለቦርድ ከመቅረቡ በፊት ይመረምራል፣

5. በየዓመቱ የተዘዋዋሪ ፈንድ ሂሳብን ኦዲት ያስደርጋል፤ ውጤቱንም በመገምገም ለኤጀንሲው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## ክፍል አምስት

## የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 31. የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ

1. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የክፍያ መጠየቂያ ቅጽ በማሳተም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል ለህክምና ተቋማት ያከፋፍላል፣

2. የተዘዋዋሪ ፈንድ መጠንና ድርሻ በማጥናት ለቦርድ ያቀርባል፣ ሲወሰንም ለሚመለከታቸው አካላት በደብዳቤ ያሳውቃል፣

3. የተዘዋዋሪ ፈንድ የማዋጣት ግዴታ ያለባቸውን አካላት መክፈል ያለባቸውን የአስተዳዳሪያዊ ወጪ ድርሻ በማስላት በየሦስት ወሩ ለቦርድ ያቀርባል፣ ሲወሰንም ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንዲከፍሉ በማሳወቅ ያረጋግጣል፣

4. ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ አንድ ተወካይ ይመድባል፣

5. የትራፊክ ፖሊስ የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት የመጠየቂያ፣ የትራፊክ ፖሊስ የአደጋ ሪፖርት መስጫ፣ እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶችንና ቅጾችን በማዘጋጀትና በማሳተም ያሰራጫል፣

6. የሩብ አመትና ሌሎች ሪፖርቶችን የአገልግሎት ክፍያ መረጃ የሚያዝበት የባሕር መዝገብ ያዘጋጃል፣ ሌሎች ለኦዲት ስራ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን በአግባቡ ይይዛል፡፡

### 32. የመድን ሰጪ ኩባንያዎች

1. ለአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ክፍያ የሚሆን መዋጮ (ለተዘዋዋሪ ፈንድ የሚከፈል ድርሻ) በየሩብ አመቱ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስም በተከፈተው የሂሳብ ቁጥር ገቢ ያደርጋል፡፡

2. በተከፈተው የሂሳብ ቁጥር ገቢ ያደረጉትን ገንዘብ መጠን የሚያሳይ የባንክ ደረሰኝ ኮፒ ለኤጀንሲው ይልካሉ ወይም ያሳውቃሉ፡፡
3. ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ አንድ ተወካይ ይመድባሉ፡፡

## 33. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

1. በዚህ መመሪያ በተገለጸው መሰረት ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት ክፍያ የሚሆን መዋጮ የሚመሰረተውን ተዘዋዋሪ ፈንድ የሚቀመጥበትን የባንክ ሂሳብ በመክፈት ቁጥሩን ያሳውቃል፣ ለክልልና ለከተማ አስተዳደሮች የጤና ቢሮዎች ይደለድላል፣ ያስተዳድራል፣
2. ሚኒስቴሩ የሚያስተባብራቸው ሁሉም ባለድርሻ አካላት አሰራሩን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባር ከኤጀንሲው ጋር በጋራ ይሰራል፣
3. በየሩብ ዓመቱ ስለሰራ አፈፃፀሙ የስራ ግምገማ ያደርጋል፣ ውጤቱንም ለባለድርሻ አካላት ከኤጀንሲው ጋር በመሆን ያቀርባል፣
4. የክልል የጤና ቢሮ የሕክምና ተቋማት የከፈሉት የአገልግሎት ክፍያ መጠየቂያና አባሪ ሰነዶችን ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ያስተላልፋል እንዲሁም ክፍያውን የሚገልጽ የሩብ ዓመት ሪፖርት ለኤጀንሲው ያቀርባል፣
5. ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ አንድ ተወካይ ይመድባል፡

## 34. የጤና ቢሮ

1. ከአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት ሰጪ የህክምና ተቋማት የተላከለትን የወጭ ሰነድ አጣርቶ በዚህ መመሪያ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ክፍያ እንዲከፈል ያደርጋል፣
2. ከህክምና ተቋማት የተላከለትን የወጪ ሰነድ አጣርቶ ክፍያ ከፈጸመ በኋላ ሰነዶቹን ለጤና ጥበቃ ሚ/ር በወቅቱ ያስተላልፋል፣

3. ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትና የህክምና ተቋማት የዚህን መመሪያ ይዘት እንዲያውቁትና በአግባቡ ተግባራዊ እንዲያደርጉት አስፈላጊውን ተግባር ይፈጽማል፣

4. የሩብ ዓመት የክፍያ አፈጻጸም መግለጫ ሪፖርት በማዘጋጀት ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በዚህ መመሪያ ላይ በተገለጸው ጊዜ ይልካል፣

## 35. የወረዳ ጤና ጽ/ቤት

ከጤና ተቋማት የሚመጡ የአስቸኳይ ህክምና ጥያቄዎች አረጋግጦ ከጤና ቢሮ ጠይቆ ይከፍላል፡፡ በተለይም፣

1. በሀገሪቱ ውስጥ ያለ ማንኛውም የሕክምና ተቋም በመንገድ ላይ አደጋ ተጎጂ ለሆነ ማንኛውም ሰው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የአስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ በአዋጁ የተቀመጠውን ድንጋጌ እና ይህን መመሪያ ተግባራዊ እንዲያደርጉ በስሩ ያሉትን የህክምና ተቋማት ይቆጣጠራል፣

2. አስቸኳይ የሕክምና አገልግሎት በአደጋው ቦታ ወይም በአምቡላንስ ውስጥ እንዲሁም በሕክምና ተቋም ውስጥ ባለ የድንገተኛ ክፍል ውስጥ ለተጐጂው የሚደረግ የሕክምና አገልግሎት ወጭዎችን በሙሉ በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰውን የብር 2000 የአስቸኳይ የሕክምና ወጭን ይሸፍናል፡፡

3. ታካሚው በሆስፒታል ውስጥ ተኝቶ ወይም በተመላላሽነት እንዲታከም የህክምና ባለሙያው ውሳኔ ሲሰጥ የአስቸኳይ የህክምና አገልግሎቱ ይቋረጣል፣ቀጣይ ህክምናን በተመለከተ ተጎጂው እና የጤና ተቋሙ ከመድን ፈንድ ወይም ከሌሎች መድን ሰጪዎች ጋር በመነጋገር የሚቀጥል ይሆናል፣

## 36. የሕክምና ተቋማት

1. እስከ ብር 2000 ድረስ የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፣

2. የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት መጠየቂያ ቅጽ በመጠቀምና አባሪ ሰነዶችን በማያያዝ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለህክምና ያወጡት ወጭ እንዲከፈላቸው ለወረዳ የጤና ጽ/ቤት ማቅረብ አለባቸው፣

3. በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማሰባሰብ አለባቸው፡፡

## 37. ፖሊስ ወይም የትራፊክ ፖሊስ

1. ማንኛውም የትራፊክ ፖሊሰ የተሽከርካሪ አደጋ በደረሰ ጊዜ በኤጀንሲው የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ተጎጂው ወደ ህክምና ተቋም እንዲሄድ ያደርጋል፣

2. የተሽከረካሪ አደጋ በደረሰ ጊዜ በቦታው ወይም በስፍራው የትራፊክ ፖሊስ ሳይኖር ተጎጂው ወደ ህክምና ተቋም የተወሰደ ከሆነ ፖሊስ የተሽከርካሪ አደጋ መድረሱን አጣርቶ ለህክምና ተቋሙ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

## 38. ሌሎች አካላት

መድን የገባው ሰው፣ የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም አስተዳዳሪ፣ አደጋውን ያደረሰው አሽከርካሪ፣ ስለአደጋው እንደሁኔታው ለኤጀንሲው ወይም ለመድን ሰጭ ኩባንያው በ10 ቀን ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

# ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ

## 39. ቅሬታ አቀራረብ

1. ማንኛውም የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት የህክምና ተቋም ወይም ጉዳት የደረሰበት ሰው በዚህ መመሪያ በተገለጸው አሰራር መሰረት ባይፈጸምለትና ቅሬታ ቢኖረው ለአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎት አፈጻጸም ተቆጣጣሪ የጋራ ኮሚቴ ወይም ለኤጀንሲው ማቅረብ ይችላል፤

2. የጋራ ኮሚቴው ወይም ኤጀንሲው የቀረበለትን ቅሬታ በማጣራት በ10 ቀናት ውሰጥ መልስ ይሰጣል ወይም ሰፊ ጊዜ የሚያስፈልገው ከሆነ ተገቢውን ማጣሪያ በማድረግ መልስ የሚሠጥበትን ጊዜ ያሳውቃል፡፡ ይሁን እንጂ ማንኛውም ቅሬታ በቀረበ በ30 ቀናት ውስጥ አመልካቹ መልስ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

## 40. የተጭበረበሩ ሰነዶችና የሀሰት የክፍያ ጥያቄዎች

ማንኛውም አካል ለሚያቀርበው ሀሰተኛ ሰነድ ወይም ለሚጠይቀው የሀሰት የክፍያ ጥያቄ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በወንጀልና በፍትሐብሔር ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 41. መመሪያን ስለመሻር

የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎትን በተመለከተ ከዚህ በፊት የወጣው የአስቸኳይ ህክምና አሰጣጥና ከጤና ተቋማት ጋር የሚኖረው የስራ ግንኙነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 በዚህ መመሪያ ተሸሯል፣

## 42. መመሪያ ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 43.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 10 ቀን 2006 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

ወርቅነህገበየሁ

የትራንስፖርትሚኒስትር